# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ቁጥር 166 ሃምሌ 14 2003 ገጽ 1

**"ወይን-ለመኖር" የኢትዮጵያን ህዝብ ያዋረደ፤ ለትውልድ የሚተርፍ የማኅበራዊ ስነልቦና ኪሳራ የሚያደርስ፤ ደካማውን ወያኔን ጠንካራ በማስመሰል የህዝባችንን የትግል ሃሞት የሚያፈስ እኩይ ተግባር ነው። አንድ ኢትዮጵያዊ በወያኔ አባልነቱ የሚያገኘው ጥቅም "ራሱን ለባርነት የሸጠበት ዋጋ ነው" ከማለት ሌላ ምን ትርጉም ይሰጠዋል?**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## በአዲስ አበባ ከተማ እየታየ ያለው ዝርፊያ ተስፋፍቶ ቀጥሉአል፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አምስት ኪሎ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሁለት ቤተ ሙከራዎች ባልታወቁ ሰዎች ተዘረፉ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተደራጁ ሃይሎች የጦር መሳሪያን በመጠቀም ሰፊ የሆነ ዘረፋ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እየፈጸሙ መሆኑ ተደጋግሞ የተዘገበ ሲሆን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ባወጣው ዘገባው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ የትምህርት ክፍል ሥር የሚገኘው ሲስኮ ላብራቶሪ በሩ በድሪል ተበስቶና ተከፍቶ መዘረፉ ታውቁአል፡፡ይህ ላብራቶሪ ከተዘረፈ ከሦስት ቀን በኋላ፣ ደግሞ አይአይቲ ደልሂ የተባለው የማስተርስ ተማሪዎች ላብራቶሪም እንዲሁ መዘረፉ ታውቁአል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚታየው የተደራጀ ዝርፊያ ህብረተሰቡን ስጋት ላይ የጣለ ጉዳይ ሆኗል ያለው ኢሳት በአገሪቱ ውስጥ የሚታየው የኑሮ ውድነት መባባስ እና የደሀው ቁጥር ከቀን ወደ ቀን መበራከት ዝሪፊያውን እንዳባባሰው ለማወቅ መቻሉንም አክከሎ ገልጹአል።

እንደ ኢሳት ምንጮች ዘገባ በአዲስ አበባ ከተማ እየታየ ያለውን የተደራጀ ዝሪፊያው ከጀርባ ሆነው ከሚመሩት መካከል ነባር የህወሀት አባላትም እንደሚገኙበት፣ እነዚሁ አባላት የተለያዩ መጠን ያላቸውን የጦር መሳሪያዎች ላደራጁአቸው ሃይሎች በመስጠት በእጅ አዙር ዝሪፊያ ላይ መሰማራታቸውን ህብረተሰቡ ጠንቅቆ እንደሚያውቅ ታውቁአል።

ቃሊቲ ውስጥ በተደራጀ ዝሪፊያ ታስረው ከሚገኙት መካከል አብዛኞቹ የህወሀት አባላት መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ ያለው ኢሳት አባላቱ በእንዲህ አይነት ዝሪፊያ ውስጥ ለምን ለመሰማራት እንደፈለጉ የሚታወቅ ነገር እንደሌለም አክሎ ገልጹአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በምርጫ ዘጠና ሰባት በአዲስ አበባ ከተማ የማያዳግም ቅጣትን ከቀመሰ ወዲህ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን በተለያዩ መንገዶች መበቀል መቀጠሉ በስፋት የተዘገበ ሲሆን በ 1997 ምርጫ ማግስት ዘራፊዎች የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብን ሲያስቸግሩ ሂዱና ቅንጅትን ጥሩ ቅንጅት ያድናቺሁ የሚል መልስ እየተሰጣቸው እንደነበረና ከነዚህም ዘራፊዎች አብዛኞቹ ሴረኛው ወያኔ አሰማርቱአቸው የነበሩ መሆኑ መዘገቡ አይዘነጋም።

## የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ከተቃዋሚዎች ይወግናል በማለት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለአሜሪካ መንግሥት በማስረጃነት ያቀረበው ባለ 42 ገጽ አቤቱታ አፈትልኮ ለህዝብ ይፋ ሆነ

የህዝባችንን መረጃ የማግኘት መብት በማፈን የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም እየተወራጨ ያለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፤በቅርቡ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ለተመለሰው የአሜሪካ ድምጽ የአስተዳደር ቦርድ ያቀረበው ባለ 42 ገጽ አቤቱታ ለህዝብ ይፋ መሆኑን የግንቦት 7 ዜና ዘጋቢ ገለጸ።

በወጣቱ የዲሞክራሲ አክቲቪስትና ጋዜጤኛ አበበ ገላው አማካይነት አዲስ ቮይስ በተባለው ድህረገጽ ላይ የወጣው ይህ 42 ገጽ የወያኔ አቤቱታ ፤ የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ የአማሪኛው ዝግጅት ክፍል እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከጃንዋሪ 13 እስከ ሜይ አሥራ አንድ 2011 ፤ወይም እንደ ኢትዮጵያዊን አቆጣጠር ከጥር እስከ ግንቦት 2003 ዓም ከተላለፉት ዝግጅቶች ውስጥ "ወያኔ ተቃዋሚዎቼ ናቸው" ካላቸው 31 ሰዎች ጋር የተደረጉ ቃለመጠይቆች ወይም አስተያየቶች ትራንስክሪፕት እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

ከአማሪኛ ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉሞ ለአሜሪካ መንግሥት በቀረበው በዚህ 42 ገጽ ማስረጃ ላይ የተሰጡ አስተያየቶች በአብዛኛው፤ በቱኒዚያና በግብጽ የተካሄዱ ህዝባዊ አብዮቶችን የቀሰቀሱ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በሙሉ በአገራችን ውስጥ መኖራቸውን የሚያመላክትና የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቶሎ ማሻሻያ እርምጃዎችን ካልወሰደ በቀር በራሱ ላይ አደጋ እየጋበዘ መሆኑን ከማስጠንቀቅ ያለፈ መልዕክት እንደሌለው ታውቆአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በአባይ ግድብ ግንባታ ሽፋን ዜጎችን መዝረፉን ቀጥሉአል፣ የግል ትመህርት ተቋማት በግዴታ የተጣለባቸውን ገንዘብ መክፈል አንችልም እያሉ ነው

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለአባይ ግድብ ማሰሪያ በውዴታ ግዴታ ገንዘብ እንዲለግሱ ከጠየቀ ወዲህ ፣ ተቋማቱም የተጣለባቸውን እዳ የከፈሉ ቢሆንም ዘራፊው የወያኔ አገዛዝ የከፈላቺሁት መጠኑ አነስተኛ ነው በሚል በድጋሚ እንዲያዋጡ ማዘዙን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት የግል ተቋማቱ 30 ሚሊዮን ብር ማዋጣት እንዳለባቸው ዘራፍፊው አገዛዝ የግዴታ ትእዛዝ መስተላለፉ የታወቀ ሲሆን፣ ተቋማቱ ግን ይህን ያክል ገንዘብ ለመክፈል እንደማይችሉ ግልጽ በማድረጋቸው ውዝግብ የተፈጠረ ሲሆን ይህን የተነሳውን ውዝግብ በድርድር ለመፍታት በሚል ሽፋን በተደረገው ማስፈራራትና ዛቻ ተቁአማቱ ቀደም ብሎ በግድ እንዲከፍሉ የተጠየቁት የ30 ሚሊዮን ብር ወደ 20 ሚሊዮን ብር ዝቅ ሊል እንደቻለ ታውቁአል።

በዚህም ምክንያት በወንበዴው አገዛዝ የገንዘብ ክፍያ የግዴታ ጫና የተጣለባቸው የግል ትምህርት ተቋማት ይህን ገንዘብ ለማሙዋላት እየተተራመሱ እንደሚገኙ ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ከስራ የተባረሩ የቴሌኮሚዩኒኬሽን ሰራተኖች ከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸው ታወቀ

ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽን መስሪያ ቤት ወደ ኢትዮ ቴሌኮም ከተቀየረ በኋላ በርካታ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ከስራቸው እንዲሰናበቱ የተደረጉ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን እነኝህ ከስራ የተባረሩ ሰራተኖች ከነቤተሰቦቻቸው ከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸውን ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ የጥቃቱ ሰለባ ሰራተኞች ገልጸዋል።

አንዲት ለገሃር በሚገኘው የቴሌኮሚዩኒኬሽን ጽ ቤት በጸሃፊነት ለበርካታ ዓመታት ያገለገሉ የስራ ተፈናቃይ እንደገለጹት ቴሌ ከጸሐፊ እስከ ከፍተኛ ክፍል ኃላፊነት የሥራ ደረጃ የደረሱ የበርካታ ዓመታት የስራ ልምድ ያላቸውን ሠራተኞች ማባረሩንና ሁሉም ለማለት በሚቻል ደረጃ ቤተሰብና በርካታ ልጆችም ያሏቸው በመሆኑ ከፍተኛ ችግር ላይ እንደወደቁ በምሬት ገልጸዋል። ወይዘሮዋ እንደገለጹት፣ ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙዩኒኬሽን ኮርፖሬሽን ወደ ኢትዮ ቴለኮም ይቀየራል የሚል ወሬ ሲናፈስ ጀምሮ አሁን የደረሰባቸው እጣ ፈንታ ሊደርስባቸው እንደሚችል (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የንግዱ ማህበረሰብ ማዋከቡን ቀጥሏል፣ መርካቶ ውስጥ ከ450 በላይ ንግድ ቤቶች ታሸጉ

በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ አንድና ስምንት ውስጥ ከ450 በላይ የንግድ ቤቶች ያለንግድ ፈቃድ ሰርታችሁዋል በሚል ምክንያት መታሸጋቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዝን ኢሳት የውስጥ ምንጮቹን በመጥቀስ የዘገበ ሲሆን ዘረኛውና ጨካኙ የወያኔ አገዛዝ የወሰደው ርምጃ ነጋዴዎቹን እጂግ ማበሳጨቱን ተያይዞ የደረሰው ዜና አመልክቷል። ከዚሁ ጋር ተያይዞም ባሁኑ ሰአት በንግዱ ማህበረሰብ ከፍተኛ የሆነ ግብር በመጣልና እንዲሁም ለአባይ ግድብ ግንባታ ከፍተኛ ገንዘብ ካላዋጣችሁ በማለት ለከፍተኛ ምሬት እየዳረጋቸው መሆኑ ታውቋል። ኢሳት ዘጋቢውን ዋቢ በማድረግ እንደገለጸው ቀድሞ 300 ብር ይከፍል የነበረ ነጋዴ በአሁኑ ሰአት ከ7 እስከ 8 ሺ ብር ክፈል እንደሚባል ታውቋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ግብሩን የሚጥሉት የአገዛዙ ባለስልጣናት በዘር ሃረግ፣ በዘመድ አዝማድ፣ በድርጅት አባልነትና በመሳሰሉት የሚሰሩና ከፍተኛ የሆነ አድሎ እየፈጸሙ በመሆናቸው በህዝቡ ላይ በደልን ይፈጽማሉ በማለት ነጋዴዎች እንደሚናገሩ ኢሳት በዘገባው ላይ አክሎ ገልጿል።

የነጋዴው ማህበረሰብ ባሁኑ ሰአት እየተጣለበት ያለው ከአቅም በላይ የሆነ የግብር ጥያቄ እሮሮ በአዲስ አባባ ከተማ ብቻ ሳይሆን በመላ ሃገሪቱ በሚገኙት ሌሎችም ክልሎች እንደሆነ ታውቋል። በአማራ ክልል የሚገኙ ነጋዴዎች የክልሉ ባለስልጣናት ተገቢ ያልሆነ ግብር እየጣሉ ድርጅቶቻቸው እንዲዘጉ እንደሚያደርጉዋቸው በተደጋጋሚ ለኢሳት መግለጻቸውንም ዘገባው አመልክቷል።

እንደ ኢሳት ዘገባ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ጠላ የሚሸጡ አነስተኛ ነጋዴዎች ሳይቀሩ የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ በመጠየቃቸው ከፍተኛ የሆነ ትርምስ እንደተፈጠረ ነዋሪዎች እየተናገሩ መሆኑ ታውቋል።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለው የዋጋ ንረት አሁንም እንደቀጠለ መሆኑን በአዲስ አበባና ሌሎች ትላልቅ የክልል ከተሞች ተዘዋውሮ የተመለሰው ሪፖርተራችን ገልጾአል። እንደ ሪፖርተራችን ዘገባ የእህል ዋጋ ከአለፈው ወር ጋር ሲነጻጸር እስከ 50 በመቶ ጭማሪ ከማሳየቱ ጋር ተያይዞ የህዝብ የመግዛት አቅም እጅግ እየወረደ መምጣቱና የወያኔ አባልና አጋር (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# የወያኔ የአባልነት ደብተርን በመቅደድ ነፃነትን ማወጅ፤ ዛሬ!!!

በዚህ ሳምንት ከወደ ሰሜን ሸዋ ባጭሩ እንዲህ የሚል መልካም ዜና ተሰምቷል።

*በሰሜን ሸዋ ዞን በኤፍራታና ግድም ወረዳ የኢህአዴግን ስብሰባ አንሳተፍም ያሉ የኢህአዴግ አባላት የነበሩ መምህራን የ8 ቀናት ደመወዛቸው መቀጣታቸውና ከሐምሌ ወር ደመወዛቸው ተቀናሽ እንደሚሆን የሚገልጽ ደብዳቤ ደረሳቸው። መምህራኑ ለደብዳቤው በቃል የሰጡት ምላሽ "ለወደፊቱም በኢህአዴግ ስብሰባ አንካፈልም፤ ራሳችንን ከአባልነት አግልለናል" የሚል ሆኗ። በዚህ ምላሽ የተበሳጩት የኢህአዴግ ባለሥልጣናት በስብሰባ የማይሳተፉና ከድርጅቱ የሚወጡ ከሆኑ ከሥራ እንደሚባረሩ ማስጠንቀቂያ ሰጧቸው። መምህራኑ ግን "የሚመጣውን ለመቀበል ተዘጋጅተናል" አሉ።*

ይህ ታላቅ ብሥራት ነው!!!

"ወይን-ለመኖር" የሚል ስላቃዊ ስያሜ የተሰጠው ለጥቅም ሲባል የወያኔ አባል መሆን፤ በገዛ ራስ ፈቃድ ባርነት መቀበል በመሆኑ ህሊና ያለው ዜጋ ሁሉ ሊዋጋው የሚገባ መሆኑን ከዚህ በፊትም ያነሳነው ጉዳይ ነው። "ወይን-ለመኖር" የኢትዮጵያን ህዝብ ያዋረደ፤ ለትውልድ የሚተርፍ የማኅበራዊ ስነልቦና ኪሳራ የሚያደርስ፤ ደካማውን ወያኔን ጠንካራ በማስመሰል የህዝባችንን የትግል ሃሞት የሚያፈስ እኩይ ተግባር ነው። አንድ ኢትዮጵያዊ በወያኔ አባልነቱ የሚያገኘው ጥቅም "ራሱን ለባርነት የሸጠበት ዋጋ ነው" ከማለት ሌላ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? የሰሜን ሸዋ መምህራን "በወይን-ለመኖር" ላይ የመጀመሪያን ህዝባዊ ጡጫ በማሳረፋችሁ "እንኳን ደስ ያላችሁ!!!" እንላችኋለን። ኮርተንባችኋል!!!

እንደሚታወቀው "በወይን-ለኑሮ" ዘይቤ ራሱን እያታለለ ወያኔን የተቀላቀለ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከሚከተሉት ቢያንስ በአንዱ መንገድ መተባበሩ አይቀርም።

**1. በስለላ መተባበር**

የወያኔ ድርጅቶች የስለላ ተቋማት ናቸው። የወያኔ አባላት እርስ በእርሳቸው፣ ጎረቤቶቻቸውና የሥራ ባልደረቦቻቸውን እንዲሰልሉ ይደረጋል። የወያኔ አባል መሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዚህ አጸያፊ ተግባር መሳተፍ ማለት ነው።

**2. በዝርፊያ መተባበር**

ለትናንሽ ጥቅሞች ተብሎ የወያኔ አባል በተሆነ ቁጥር ወያኔ የዝርፊያውን አድማስ ያሰፋል። በትንሹ እንኳን የጥቅም ተካፋይ የሆነ ሰው ትልቁን ዘረፋ የመቃወም የሞራል ብቃት አይኖረውም ። በዚህ የተበረታታው የወያኔ ዘረፋ እየሰፋ መጥቶ እነሆ የእርሻ መሬቶችን ለባእዳን ቱጃሮች እስከ መሸጥ ደርሷል።

**3. በዝምታ መተባበር**

የወያኔ ድርጅቶች በራሳቸው አባላትም በህዝብም ልብ ውስጥ ፍርሃትን የሚረጩ መርዞች ናቸው። በፍርሃት ሳቢያ በርካታ ዜጎቻችን ያዩትን እንዳላዩ፤ የሰሙትን እንዳልሰሙ ማለፍን ለምደዋል። በዚህም ምክንያት አድርባይነትና እኖርባይነት በአስደንጋጭ ፍጥነት እየተስፋፉ ናቸው። ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንዲህ ዓይነት ስነልቦና በተላበሱ ዜጎች ልትገነባ አትችልም።

ከዚህ አዋራጅ ስነ-ልቦና የምንወጣበትን መንገድ የሰሜን ሸዋ መምህራን አሳይተውናል። መምህራኑ "ለጥቅም ወይም በፍርሃት ምክንያት የወያኔ አባል በመሆን ባርነትን አንቀበልም" ብለዋል። የወያኔን የአባልነት ደብተር በመወርወር ነፃነታቸውን ተቀዳጅተዋል። ይህ ነው እያንዳንዱ ህሊና ያለው የወያኔ አባል ሊያደርገው የሚገባ ተግባር።

ዛሬ ይህንን ታላቅ እርምጃ ደፍረው የወሰዱ ጥቂቶች ናቸው፤ ነገ ግን በየአደባባዩ የሚታይ ትዕይንት ይሆናል። በሊቢያ የጋዳፊን "አረንጓዴ መጽሃፍ" መቅደድ፣ መረጋገጥና ማቃጠል የምሬት መግለጫ እንደሆነ ሁሉ እኛም ዘንድ የወያኔ ኢህአዴግ የአባልነት ደብተሮች፣ ፎርሞችና ወረቀቶች በአደባባይ የሚቃጠሉበት ጊዜ እሩቅ አይደለም። ቀድመው ያደረጉት ግን ጀግኖች ናቸው።

እናም ልቦና ያላችሁ የወያኔ አባላት ዛሬ የአባልነት ደብተሮቻችሁን ቅደዱ!!! ይህንን በማድረግ ከህሊናችሁ መታረቅ እና ራሳችሁን ከባርነት ማላቀቅ ትችላላችሁ። ይህንን ተግባር ዛሬ ስትፈጽሙት ጀግኖች ናችሁ፤ ነገ ግን ተራ ነገር ይሆናል። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ በይፋ መቀደዱ የማይቀርን ወረቀት በመቅደድ ለራሳችሁ ታሪክ ስሩ።

በዚህ አጋጣሚም "የወያኔ የአባልነት ፎርም አንሞላም" በማለት ከክልሉ የወያኔ ሹማምንት ጋር ተፋጠው ላሉት የትግራይ መምህራን ያለንን አክብሮት እንገልፃለን።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለእንዲህ ዓይነቱ ለሙብትና ለነጻነት ለሚወሰዱ እርምጃዎች ትልቅ ዋጋ የሚሰጥ መሆኑን፤ ይህንንም ለሚያደርጉ ወገኖች ከፍተኛ ክብር እንዳለው እና እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎችን በቅርበት የሚከታተል መሆኑን ያሳውቃል።

**በወያኔ አባልነት ስም የዜጎች ባርነት ይብቃ!**

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጊዴስ!!!**

---

## የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ከተቃዋሚዎች ይወግናል በማለት

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በልማታዊ መንግሥትነት ሽፋን ሥም ዕድገትና መልካም አስተዳደር እያስፈንኩ ነው በማለት ለ20 አመታት ሲደሰኩር የነበረው የመለስ በረከት አገዛዝ ፤ የህዝባችን የኑሮ ደረጃ ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ፤ ህዝባዊ ብሶቱ እየተጠናከረ በመምጣቱ ስለ ቱንዚያና የግብጽ አብዮት ማውራት አበው "በዶሮ ፊት ስለፈንግል በሽታ አይወራም" የሚሉት አይነት እየሆነበት መምጣቱን ይህ ለአሜሪካ መንግሥት ያስገባው አቤቱታ ይመሰክራል ብሎአል ዘጋቢያችን ።

የፕሬዝዳንት ባራክ አባማ አስተዳደርን በመወከል ወደ ኢትዮጵያ ተጉዞ የተመለሰው የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአስተዳደር ቦርድ ልዑካን ቡድን፤ ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የቪኦኤን ስርጭት ከማስተጓጎል የሚታቀብበትን መንገድ ለመሻትና በመስኩ ትብብር ለማስፋት አልሞ እንደነበር መገለጹ የሚታወስ ሲሆን ፤ በረከት ስምዖን ለልዑካኑ ቡድን ያቀረበውን "ተቃዋሚዎቻችንን ማስተናገድ አቁሙ" ጥያቄ ለህዝብ ይፋ ያደረጉ ባለሥልጣን ለትንሽ ጊዜ ከሥራ ገበታቸው ታግደው እንደነበረ መዘገቡ ይታወሳል። ሆኖም ኢትዮጵያዊያን ባሰሙት ተቃውሞና ባደረጉት ግፊት ሰውዬው ወደሥራ ገበታቸው የተመለሱ ቢሆንም የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛው ዝግጅት ክፍል እራሱን በራሱ ሳንሱር እንዲያደርግ እየተፈጠረበት ያለውን የውስጥ ጫና ለመቃወም በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የተጠናከረ ዘመቻ መጀመራቸውን ለማወቅ ተችሎአል። በዚህ የተቃውሞ ዘመቻ ኢትዮጵያዊያኑ ለአሜሪካ መንግሥት የህግ አውጭና ህግ አስፈጻሚ አካላት በሙሉ አቤቱታ ከማሳማት ጀምሮ አስፈአጊ ሆኖ ከተገኘ ጉዳዩን በህግ ፊት እስከማቅረብ የሚዘልቅ እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀታቸው ታውቆአል። ለህዝባቸውና ለአገራቸው ነጻነት የሚቆረቆሩ ኢትዮጵያዊያን ቪ ኦ ኤ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ያቀርብ የነበረውን በ እውነት ላይ የተመሰረተ ገለልተኛ መረጃ ለህዝባችን ማሰራጨቱን እንዲቀጥል ግፊት ለማድረግ የመጀመሪያቸው በሚሆን ይፋ እርምጃ የፊታችን ጁላይ 25 በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጽቤት ፊት ለፊት ታላቅ ህዝባዊ የተቃውሞ ሰልፍ አዘጋጅተዋል።

ወያኔ ከአራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ህዝባችን በከፍተኛ የረሃብ አለንጋ ውስጥ ሆኖ ህጻናትና አረጋዊያን እንደቅጠል መርገፍ በጀመሩበት በዚህን ሰዓት ሳይቀር ከውጪ ወደ አገር ቤት የሚተላለፉቱን የሬዲዮና የቴለቪዥን ስርጭቶችን በየዕለቱ በብዙ መቶ ሺ ዶላር የሚገመት ገንዘብ ወጪ በማድረግ መጥለፉን ቀጥሎበታል።

አንባቢዎቻችን በሰሜን አሜሪካ በዋሽንግተን ዲስና አካባቢዎ የሚትገኙ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ጁላይ 25 ከአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጽ.ቤት ፊት ለፊት በተጠራው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ በመገኘት ድርጊቱን እንዲታወግዙ የዝግጅት ክፍላችን የበኩሉን አገራዊ ጥሪ ያቀርብላችኋል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በአባይ ግድብ ግንባታ ሽፋን

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተያያዘ ዜና የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ተብሎ የሚዋጣው መዋጮ በህበረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታና ተቃውሞ እያስከተለ በመምጣቱ አገዛዙን እጅግ ስላሰጋው ያለውዴታ በግዴታ የወር ደመወዛቸውን እንዲለቁ ለተደረጉት መንግሥት ሠራተኞች የተወሰደባቸው ገንዘብ ወደ ቦንድ ግዢነት እንዲለወጥላቸው ማስታወቁን ዘግቦአል። የሚሊኒየም ግንባታ ተብዬው ቦርድ ሃላፊ ከሆነው በረከት ስምዖን ቢሮ የተሰጠውን ማስታወቂያ ዋቢ በማድረግ ዜናውን የዘገበው ኢሳት ፤ የዘረኛው አገዛዝ ላለፉት 3 ወራት የመንግስት ሰራተኞች የአንድ ወር ደሞዛቸውን እንዲሰጡ ሲያስገድድ መቆየቱን አውስቶ ፣ ዜጎችን ያለውዴታቸው ማስገደዱ ከቀጠለ የህዝቡ ምሬት እየጨመረ አደጋውም የዚያን ያክል ከፍ ሊል ይችላል በሚል ስጋት መዋጮ የሚለውን ሀሳብ ለመሰረዝ እንደተገደደ ከአስተያየት ሰጪዎች መረጃ ማሰባሰቡን አክሎ ገልጹአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለያዩ አቅጣጫዎች የተፈጠረበትን ጫናና ውጥረት ያረግብልኛል በሚል በአዲስ ነጠላ ዜማነት የለቀቀው የአባይ ግድብ ዜማ የአንድ ሰሞን እስክስታ ብቻ ሆኑ መቅረቱና ኢትዮጵያዊያን የወያኔን ማዘናገያ በመገንዘባቸው ለግድብ ስራው ምንም አይነት ገንዘብ መክፈል እንደማይፈልጉ እየገለጹ መሆናቸውን ቀደም ብለን መዘገባችን አይዘነጋም።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የንግዱ ማህበረሰብ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ድርጅቶች አባላት ሳይቀሩ በኑሮ ውድነቱ እየተማረሩ መምጣታቸው ታውቋል። የምግብ እህሎች የዋጋ ጭማሪ በተለይም በደሃው የህብረተሰብ ክፍል ላይ እጂግ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩንና ኑሮም ሰቆቃ እየሆነባቸው መምጣቱን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቶአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በምርጫ 97 በህዝብ መተፋቱን ከተረዳ ቦኋላ በተለይም በዝረራ በተሸነፈበት የአዲስ አባባ እና አንዳንድ ትላልቅ የአገሪቱ ከተሞች ህዝብ ላይ የብቀላ እርመጃ በመውሰድ ሆን ብሎ ምሬትንና ጉስቁልናና እያስፋፋ መሆኑ ሲገለጽ ቆይቶአል። በወቅቱ ለቅንጅት ድጋፋቸውን ሰጥተው የነበሩ የንግዱ ህብረተሰብ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ግልጽ የሆነ ጥቃት እየደረሰባቸው እንደሆነ ሲታወቅ ከገቢያቸው በላይ ግብር እንዲቆለልባቸውና የያዙትን የንግድ ድርጅት ማንቀሳቀስ ተስኖአቸው ከውድድር እንዲወጡ እየተደረገ መሆኑ ብዙዎችን የመረረ ሃዘን ላይ ጥሎአል።

---

## መለስ ዜናዊ የወለደው ርሃብ!!!

ከዝግጅት ክፍላችን

በቅርቡ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ ውስጥ ርሃብ አለ እንዴ ተብሎ ተጠይቆ ሳያንገራግር የሚከተለውን መልስ ሰጠ፤

> "ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ርሃብ ሳይሆን
> የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ነው"።

አለ ሌባ ጣቱን ወደላይ ቀስሮ።

መለስ ዜናዊ ይህን መልስ በሰጠበት ወቅት ኦጋዴን ውስጥ ህጻናት፤ ጎልማሶችና አዛውንቶች እንደቅጠል ይረግፉ ነበር። እንዲህ ህዝቡ በርሃብ ሲያልቅ የረድኤት ድርጅቶች ወደ ኦጋዴን ገብተው በርሃብ የሚረግፈውን ህዝብ እንዳይታደጉ በመደረጉ ኦጋዴን ሰው አልባ ሆነች።የኦጋዴን ህዝብ ዘር ሆን ተብሎ እንዲጠፋ ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል ተፈጸመበት። ይህ ሁሉ ጭካኔ በመለስ ዜናዊ አመራርና በዙሪያው በተሰበሰቡ ሆድ አደሮች አማካኝነት መፈጸሙን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ልብ ሊለው ይገባል።

የርሃቡ ነገር በኦጋዴን ብቻ ሳይወሰን በኦሮሚያ፤ በደቡብ፤በአማራ፤ በጋምቤላ ዘልቆ አገሪቷን ሁሉ አዳረሰ። መለስ የርሃብተኞችን ቁጥር እየደበቀ ቢሰነብትም በያዝነው ዓመት 4 ነጥብ አምስት ሚሊዮን አስቸኳይ ነፍስ አድን የምግብ እርዳታ የሚጠባበቁ ርሃብተኞች እንዳሉ ተገልጿል። እነዚህ በአደባባይ የወጡና ዓለም ያወቀቻው ሲሆኑ በየጎጆው በጠኔ የሚሞቱትን ህጻናትና አዛውንቶች ቤቱ ይቁጠራቸው።

አገሪቷ መለስ ሰራሽ ችጋር ውስጥ ከመግባቷ በፊት መፍትሄ እንፈልግለት ያሉ ዜጎችን መለስ ዜናዊ በአሸባሪነት እየከሰሰ የቻለውን እየገደለ ያልቻለውን ደግሞ የሞት ፍርድ እየፈረደ በክፍ አቋሙ ጸንቷል። ዜጎቻችን የሚላስ የሚቀመስ አጥተው በየሜዳው ሲወድቁ እያየ "ርሃብ የለብንም ችግሩ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ነው መጠነኛ ገንዘብ ካገኘን ችግሩ ይቃለላል" ብሎ ተሳለቀ። መለስ ዜናዊ እንዲህ ያለውን ነገር አስቦና አውቆ ሲናገረው በዙሪያው የተሰበሰቡ ሆድ አደሮች ደግሞ ሳያስቡ ያጨበጭቡለታል። መለስም ክፍ ሃሳቡ ዋጋ ያገኘ እየመሰለው በኢትዮጵያዊያን ስቃይ ሃሴት አድርጎ እስከ ዛሬ ዘለቀ።

መለስ ዜናዊ "ገንዘብ ካገኘን ችግሩ ይቃለላል" ሲል በረሃብተኛው ሥም በየአመቱ ከምዕራባዊያን ለጋሽ አገሮች የሚጎርፍለትን ያልደከመበት ገንዘብ መዝረፍ ልማዱ በመሆኑና አንዱም የዝርፊያ መንገድ በእርዳታ የሚገኝ ገንዘብ መሆኑን ስለሚያውቅ በርሃብ የሚያልቀውን ህዝቡ ሊታደግ የሚችል ማንኛውንም ዓይነት እርዳታ ከመጠየቅ ፈንታ ጥሬ ገንዘብ ቢሰጠኝ ሲል ተመኘ። ለርሃብተኛ የሚላከውን እርዳታ መዝረፍ አሁን የጀመረው አዲስ ነገር ሳይሆን ያደገበት የኖረበትና የለመደው ዓመሉ ነው።መለስ ገንዘብ እስካስገኘና ስልጣን ላይ እስካቆየው ድረስ በዝህች ምድር ላይ የማይፈጽመው የወንጀል ዓይነት እንደሌለ የኋላ ታሪኩ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። የትግራይ ህዝብ እንደቅጠል በሚረግፍበት በዚያ ክፍ ወቅት የተገኘውን የምግብ እርዳታ ሽጦ የቻለውን በግል ባንኩ ቀሪውን ደግሞ ዘረኛና ዘራፊ ቡድኑን ይበልጥ ለማደረጃት መጠቀሙን ታሪክ መዝግቦ ይዞታል።

መለስ ዜናዊና አስተዳደሩ ርቀው ማየትና የነገውን ማሰብ የሚችል የአእምሮ ልቀት የሌላቸው በመሆኑ አገሪቷን እንዲህ ያለ ችጋር ውስጥ ዘፍቀዋታል። የመለስ ዜናዊ እኩይ አስተሳሰቡ ካልተተገበረ ቁጥሩ 12 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ አይደለም ኢትዮጵያ ራሷ ከገጸ ምድር ብትጠፋ ግድ የሚለው ግለሰብ እንዳልሆነ ሥራዎቹ ያስረዳሉ። ለዚህም አባባል ምስክር የሚሆነው የተሳሳተ ፖሊሲውን እንዲቀይር ብዙ ግዜ ሲጠየቅ *"በእኛ ሬሳ ላይ ታደርጉታላችሁ"* እያለ ሲፎክር መኖሩ ነው"። የፍከራው ውጤት የሰው ልጆች እንደቅጠል እንዲረግፉ አደረገ።ኢትዮጵያም እንደገና ስሟ በርሃብ ተነሳ ኢትዮጵያዊያንም በያሉበት አንገታቸውን እንዲደፉ ሆነ።

አገሪቷ በእንዲህ ዓይነት ችጋርና ውረደት ውስጥ እያለች ሥልጣኑን እስከወዲያኛው ማደላደል ተቀዳሚ ተግባሩ የሆነው ይህ ግለሰብ፤ ይባስ ብሎ ለአገር ውስጥ ደህንነትና ለመከላከያ ሃይሉ ከ350 ሚሊዮን ዶላር በላይ በጀት መድቧል። ከአንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ አድርጎም ሁለት መቶ ዘመናዊ የጦር ታንኮችን ገዝቷል።ይህም ግዥ ዩክሬን ከ15 ዓመታት ወዲህ የሸጠችው ከፍተኛው ሽያጭ ሁኖ ተመዝግቦላታል።በዚህም ብር ዩክሬን ህዝቧን ትመግብበታለች። ኢትዮጵያዊያንም በርሃብ ያልቃሉ። ቢያንስ ላለፉት 10 አመታት ያህል በያመቱ ከ12 ሚሊዮን ያላነሰ ርሃብተኞች ያላት አገር ከመቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ አውጥታ የጦር ታንኮች ስትገዛ ማየት የችግሩ ሰለባ ለሆነው ለኛ ለኢትዮጵያዊያኑ ብቻ ሳይሆን ስንዴና ጥሬ ገንዘብ የሚለግሱንን ባዕዳን ሳይቀር አስገርሞአል። አገሪቷ የሚያሰጋት የውጪ ጠላት ሳይኖራት ከረሃብተኛው ጉሮሮ ነጥቆ 200 ታንኮችን መሸመት፤ ከጥጋባቸው ብዛት ማመዛዘን ተስኖአቸው ጦር አውርድልን እያሉ ነጋሪት በመጎሰም ላይ ያሉትን መለስና ዘራፊ ቡድኑን የደረሱበትን እብሪት ደረጃ አመልካች ነው። ሁላችንም እንደምንረዳው እነዚህ ቡድኖች ለዚያች አገር ዳር ድንበር መከበርና ክብሯን ለማስጠበቅ ብለው ታንኮችን እንዳልገዙ የተሰወረ አይደለም። ይህ አንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር ወጥቶባቸው የተሸመቱ ታንኮች ወያኔ ራሱ በፈጠረው የኑሮ ውድነት የተዳከመው ህዝባችን ብሶት መሮት በአገዛዙ ላይ እንዳያምጽ በፍርሃት ለማርበድበድና ለማሸበር ታሳቦ እንደሆነ ጠንቅቀን እናውቃለን። መለስ የአገር ሉአላዊነትእና ዘላቅ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችለው የአገር ፍቅር ስሜት እንደሌለው፤ ሂሊናውም በጥላቻ የታወረ መሆኑ ግልጽ ነው። ፋይዳ ለሌለው ጦርነት በባድሜ የከፈልነውን መስዋዕትነት ምን ጊዜም አንረሳውም። ወገኖቻችን ተፈናቅለው ለሱዳን ተቆርሶ ከተሰጠው ሰፊ መሬታችን በተጨማሪ ለህንድና ለአረብ ከበርቴዎች እየታደለ ያለው ለም የአገራችን ክፍል ጉዳይ እጅግ ያንገበግበናል። መለስ የጦር ታንኮችን ከመግዛት ይልቅ የእርሻ ታንኮች ቢገዛ አይሻልም ነበር ወይም ደግሞ የጦር ታንኮችን ከመግዛት ይልቅ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን አስቆፍሮ ህዝቡን ከችጋር ለማላቀቅ ጥረት ማድረግ አይሻልም ነበረ ወይ ተብሎ ቢጠየቅ የጠላት ወሬ ነው ይለናል እንጂ እንደ አንድ አገር መሪ ትኩረታችንን አይጋራንም ወይንም ተገቢውን መልስ አይሰጠንም።መልስ የመስጠት ግዴታም አለብኝ ብሎ አያምንም።

እንደ ፈርኦን ልቡ የደነደነው መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያችን ምንም ዓይነት በጎ ምኞት ለህዝቡም ፍቅር የሌለውና አርቆ ማሰብ የሚችል አእምሮ የጎደለው ግለሰብ በመሆኑ ህዝባችን ተራበ የሚሉትን ዜጎች አሸባሪዎች ይላል እንጂ በበጎ አይመለከትም። እግዜር የፈጠረው ሰው እንዲህ በየሜዳው እንደምናምንቴ ነገር ወድቆ ሲቀር መለስ ቅንጣት ታክል ልቡ በሃዘን የሚነካ አልሆነም።በትንሹ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ በርሃብ አለ ጋ እየተገረፈ ባለበት በዚህ ወቅት መለስና ቡድኑ 8.4 ቢሊዮን ዶላር ከአገሪቷ አውጥተው በውጭ ባንኮች መደበቃቸው እነ መለስ ዜናዊ ማን እንደሆኑ ያሳያል። በአገራችን ታሪክ እንዲህ ዓይነት ዝርፊያ ሲፈጸም የመለስ ዜናዊ ዘመነ መንግስት በብቸኝነት ሲጠቀስ ይኖራል። ከመለስ ዜናዊ በፊት የነበሩ እንዲህ ዓይነት ዝርፊያ መፈጸማቸውን አልሰማንም ከመለስ በኃላ የሚመጣውም መንግስት እንዲህ ዓይነቱን ዝርፊያ ለመፈጸም እድሉ አይኖረውም። መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ እስከ ቆየ ድረስ ግን እንዲህ ያሉ አስገራሚ ዝርፊያዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ችጋሩም እየተባባሰ ይሄዳል እንጂ አይሻሻልም።

አገራችን እንደገና ስሟ በርሃብ ተነስቶ በሚወራበት ዘመን አዜብ መስፍን ወይም አዜብ ጎላ በአውሮፓና በአሜሪካ ገበያዎች ላይ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ወጪ አድርጋ ሽመታ ማካሄዷን የስፔኑ ጋዜጣ አጋልጧል። በዚህም በዓለም አሉ ከሚባሉ አባካኝ ሴቶች ተርታ ተሰልፋለች። ህዝቧ በርሃብ እያለቀ በሚልዮን የሚቆጠር ዶላር አውጥታ ጫማና ልብስ ስትገዛ ሰው ምን ይለኛልን የማታውቅ ጉድ በኢትዮጵያችን ላይ መንግሷ በአገራችን ውስጥ አሳፋሪ የታሪክ ክስተት በመሆን ተመዝግቧል።

እነዚህ ሰዎች በአገራችንና በህዝብ ላይ እየፈጸሙ ያሉት ነገር የወዳጅ ሳይሆን የጠላትነት ነው። ዜጎች የእርሻ መሬት አጥተው በየከተማው ሲንከራተቱ መለስና ቡድኑ ለም መሬቶችን ብቸኛ ዓላማቸው ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ለአረብና ለህንድ ነጋዴዎች ይሸጣሉ። በዚህም ተጨማሪ ተንከራታች አርሶ አደሮችን ይፈጥራሉ። ያስርቡታል፤ እንዲታረዝ ያደርጉታል፤ ቤትና መኖሪያ አልባ አድርገው በገዛ አገሩ ስደተኛ እንዲሆን ሜዳ ላይ ይጥሉታል። ይሄ ነው የነመለስ ዜናዊ ልማትና ብልጽግና።ይሄን መሰል ተግባራቸው ነው እንደጠላት የሚያስቆጥራቸው።

መለስ ለዝሪፊያው እንዲመቸው ሳያስቡ የሚያጨበጭቡለትን ሰዎች በዙሪያው አሰልፏል። ሳይስቡ የሚደግፉት ቡድኖች እያሰበ ወንጀል ከሚሰራው መለስ ዜናዊ ጋር በታሪክ ፊት እኩል ተጠያቂዎች ናቸው። እነዚህ ተባብረው አትዝረፍ የሚላቸውን አንደበት ለመዝጋት ህግ አውጥተዋል ብዙ ገንዘብም አፍስሰው ነጻ ሚዲያዎችን አፍነዋል። ከችጋር ለመላቀቅ ነጻ አስተሰሰብ ያስፈልገናል ያሉትን አሸባሪ ብለዋል።ለርሃቡ መብትሄ አለን የሚሉትን ሁሉ ጠላቶቼች ሲሉ ጠርተዋቸዋል። እነዚህ ቡድኖችና መለስ ዜናዊ ከስልጣናቸው መውረድ አለባቸው። የሞራል ዝቅተትና ዝርፊያ በዚያች አገር ውስጥ ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ እንዲያበቃ መለስ ዜናዊ ከስልጣኑ መባረር አለበት።

እንዲህ ጥቂቶች ተደራጅተው አገሪቷን ሲያዋርዱና የብዙሃኑን ስቃይ ሲያበዙ እያየ ዝም የሚል እንደምን ሁኖ ሰው ሊባል ይችላል? ሰው ማለት በወገን ላይ የሚደርስን ግፍንና በደልን ራስ ላይ እንደደረሰ አድርጎ መቆርቆር ማለት ነው። የመጽሃፍ ቅዱሱ ሙሴ የወንድሞቹን በደል አይቶ ዝም ባለማለቱ እግዚአብሄር እራሱን እስከሚገልጽለት ድረስ ለክብር አብቅቶታል። ኢትዮጵያዊም እግዚአብሄር እንዲያከብረው በወገኖቹ ላይ የሚፈጸመውን በደል እያየ ዝም ማለት የለበትም።

ነገ ልትፈጠር የምትችለውን መልካም አገር እያሰብን በጋራ ጠላታችን ላይ በአንድነት መነሳት ለነገ የምንለው ተግባር አይደለም። ከትላንትናዋ ኢትዮጵያ የተሻለችና ለሁላችንም የምትሆን አገር መፍጠር የእኛ ሥራ ነው። በልዩነቶቻችን መካከል ያሉ አንድነቶቻችንን ተንከባክበን ማሳደግ ይገባናል። መለስ ዜናዊ እንደሚያድረገው ልዩነቶቻችን የመለያያችን ምክንያቶች ሳይሆኑ የውበታችንና የአንድነታችን ጥንካሬ መገለጫዎች እዲሆኑን ኑ! አብረን ለኢትዮጵያ ትንሳኤ እንስራ። ርሃብንና ችጋርንም እናጥፋ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!!**

## የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ሃገርን እየጣሉ መኮብለላቸውን ቀጠሉ

በፍትሕ ሚኒስቴር የሕግ ጥናት ማርቀቅና ማስረፅ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለገሰ ዓለሙ ከሁለት ሣምንታት በፊት ለስብሰባ ከፍትሕ ሚኒስትሩ ብርሃን ኃይሉ ጋር ለስራ በሚል አሜሪካ ሄዶ የነበረ ሲሆን ወደ ሃገር ሳይመለስ በዚያው መቅረቱን ለአገዛዙ ቅርበት እንዳለው የሚታወቀው ሪፖርተር ጋዜጣ ዘገበ።

እንደ ሪፖርተር ዘገባ የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ የፍትህ ሚኒስትር ብርሃንና ለገሰ ብቻ ለስብሰባው ሄደው እንደነበር፣ ባለስልጣናቱም የሄዱበትን የስብሰባ አጀንዳ ሳያውቁ ከአሜሪካ ከፍተኛ የሕግ ኤክስፐርቶች ጋር እየተገናኙ ለተወሰኑ ቀናት ሲወያዩ የቆዩ ሲሆን ዳይሬክተሩ ዘመዶቸን ጠይቄ እመጣለሁ በማለት ለሚንስትሩ ከነገረ በኋላ በዚያው መቅረቱ ታውቋል።

ለገሰ ዓለሙ ቀደም ብሎ የኦሮሚያ ክልል ዳኛ ሆኖ በማገልገል ላይ እያለ በ2000 ዓ.ም. ወደ ፍትሕ ሚኒስቴር መሥርያ ቤት ተዛውሮ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የለውጥ አመራር ማስተባበሪያ ኃላፊና አሁን ደግሞ የሕግ ጥናት ማርቀቅና ማስረፅ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሆኖ እየሠራ እንደነበር ዘገባው አመልክቷል።

በዘረኛው የወያኔ አምባገነናዊና ግፈኛ አገዛዝ እየተማረሩ ሃገራቸውን ጥለው የሚኮበልሉት ኢትዮጵያዊያን ቁጥር እጅግ በርካታ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ አገዛዙን በሃላፊነት ቦታዎችና የተለያዩ የስልጣን ርከኖች ያገለገሉ ባለስልጣናት ይህን የስደተኝነት ጎራ እየተቀላቀሉ መምጣታቸው በስፋት ይታወቃል። ሆኖም ስደቱን ከተቀላቀሉ ቦኋላ ከፊሉ ከወያኔ ጋር በነበረበት ሰዓት ተባባሪ በመሆን በሰራው ወንጀል አፍሮ አንገቱን ደፍቶ ለመኖር የሚመርጥ ሲሆን አንዳንዱ ትቶት በመጣው ቤተሰቦቹ ላይ ወያኔ እርምጃ ይወስዳል በሚል ስጋት አደባባይ ወጥቶ እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል ለማጋለጥ ድፍረት ሲያጡና ሲያወላውሉ ይስተዋላሉ።

## ወያኔ በሥራ ዋስትና አስገድዶ የኢህ አደግ አባል ያደረጋቸው የመንግሥት ሠራተኞች ድርጅቱ የሚጠብቅባቸውን የአባልነት ግዴታ ላለመወጣት እያንገራገሩ ነው ተባለ

ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በምርጫ 97 በህዝብ መተፋቱን ከተገነዘበ ወዲህ በመላው አገሪቱ የሚገኙትን አብዛኛውን የመንግሥት ሠራተኞች በሥራ ዋስትና እና የደረጃ ዕድገት ሥም እያስፈራራ አባል ያደረገ ቢሆንም አባልነታቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ ከመጣው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የሚታደጋቸው ሆኖ ባለመገኘቱ በርካቶች የአባልነት ግዴታቸውን እንወጣም ማለት ከመጀመራቸውም በላይ ወርሃዊ የአባልነት ክፍያቸውንም መክፈል እንዳቆሙ የግንቦት7 ዘጋቢ የወያኔን የውስጥ ምንጮች ጠቅሶ ከአዲስ አበባ ከላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎአል።

እንደ ውስጥ ምንጮቻችን መረጃ በአገሪቱ ውስጥ ሥር እየሰደደ በመጣው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ምክንያት ከመንግሥት የሚከፈላቸው የወር ደመወዝ ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው መሠረታዊ ፍጆታ ከወር ወር የማያደርስ ሆኖ እያለ ፤ ቀደም ሲል ይፋ በሆነው የወያኔ 5 አመት መርህ ዕቅድ ውስጥ እንኳ ላልተካተተ የአባይ ግድብ ግንባታ የወር ደመወዛችሁን አዋጡ መባሉና በጉልበት ተግባራዊ መደረጉ የብዙዎቹን የኢህአደግ ተራ አባላት እጅግ አስቆጥቶአል።

የሥራ ዋስትና ለማስጠበቅና በየመሥሪያቤቶቹ የሚሠጡትን ደረጃ እደገትና የትምህርት ዕድል የመሳሰሉትን ጥቅማጥቅሞች ለማግኘት ሲሉ ድህረ ምርጫ 97 ወያኔ በከፈተው ጅምላ የአባላት ምልመላ ኢሃደግን ተቀላቅለው የነበሩት እነኚህ ዘጎች በሥር ዓቱ ላይ ያላቸው ቅሬታና ጥላቻ ሥር እየሰደደ ከመምጣት አልፎ ወያኔ ኢህ አደግ በሚጠራው የአባላት ስብሰባ ላይ ለመገኘት እንብታቸውን እየገለጹ ነው።

በአባላቱ እምቢታ የተደናገጠው የወያኔ ኢህ አደግ አመራር የአባልነት ድርሻቸውን አንወጣም በማለት በሚያንገራግሩት ላይ ከደመወዝ ቅጣት እስከ ከሥራ ማባረር ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ እየሰጠ መሆኑን ተያይዞ የደረሰን መረጃ ያመለክታል። ሰሞኑን በሰሜን ሸዋ ዞን በኤፍራታና ግድም ወረዳ ተጠርቶ በነበረው የኢህአደግ ስብሰባ ላይ አንገኝም ባሉት መምህራን ላይ የተወሰደው የደመወዝ ቅጣት የኢህ አደግ አመራር የደረሰበትን ኪሳራ ያመለክታል ያለው ዘጋቢያችን፤ መምህራኑ እያንዳንዳቸው የ8 ቀን ደመወዛቸውን መቀጣታቸውን የሚገልጽ የቅጣት ደብዳቤ እንደደረሳቸውና በአባልነታቸው የማይቀጥሉ ከሆነ ከሥራ እንደሚባረሩ እንደተገለጸላቸው ማረጋገጡን አክሎ ገልጾአል።

የመንግሥት ሠራተኞች የሆኑ የኢህአደግ አባላት እያሳዩ ባለው የባህሪ ለውጥ የተደናገጠው ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ በሁሉም ክልሎችና ሥራ ዘርፎች ላይ ያሉት አባልት እንዲገመገሙ ትዕዛዝ በመስጠቱ ሌላ ዙር ግምገማ እንደተጀመረ ለማወቅ ተችሎአል።

በደርግ የመጨረሻዎቹ የሥልጣን ዘመናት ለመኖር ብለው የኢሠፓኮ አባል ሆነው የነበሩ ሁሉ ስብሰባ ባለመሄድና ወርሃዊ ክፍያቸውን በአገባቡ ባለመክፈል የደርግን ውድቀት እንዳፋጠኑት የሚያስታውስ ዘጋቢያችን፤ በምርጫ 97 የታየውን ህዝባዊ ተቃውሞ ያበረደ መስሎት የአባላቱን ቁጥር በአንዴ ከሰባት መቶ ሺ ወደ አምስት ሚሊዮን ያስመነደገው ወያኔ የእራሱን መቃብር እራሱ እየማሰ እንደሆነ ምልክቶች እየታዩ ነው ብሎአል።

## ህወሃት በትግራይ ህዝብና በመላው አገራችን ላይ የፈጸመውን ክህደት ለህዝብ ንባብ ያበቁ የቀድሞ ታጋይ እና አመራር አባል አቶ አስገደ ገብረስላሴ ትግራይ ውስጥ የቁም እስረኛ ሆኑ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቀደም ሲል የጫካ ትግል ያካሂድ በነበረበት ወቅት አብረውት የነበሩትንና የድርጅቱን ጸረ አገርና ጸረ ህዝብ አቋም በሚገባ ከተረዱ ቦኋላ ለቀው በመውጣት ከተቃውሞው ጎራ የተሰለፉትን የቀድሞ ታጋዮች ማሳደዱን በመቀጠል አቶ አስገደ ገብረስላሴ በተከታታይ ለንባብ ባበቁአቸው መጻህፍት ምክንያት የቁም እስረኛ እንዳደረጋቸው ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አመለከተ። እንደ መረጃ ምንጮቻችን ዘገባ አቶ አስገደ ለዚህ የቁም እስር የበቁት ቀደም ብሎ ገሀዲ ቁጥር 1 ቁጥር 2 እና ቁጥር 3 በሚባሉት መጽሀፋቶቻቸው ሲሆን አቶ አስገደ ገ/ስላሴ ክሱ የቀረበባቸው አሜሪካ አገር በሚኖር ብስራት አማረ በሚባል የህወሀት የደህንንት አባል መሆኑንም ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቱአል።

እንደዜና ምንጮቻችን ሪፖርት አቶ አስገደ በመጽሀፋቸው የዚህን የደህንነት አባል ታሪክና የሰራቸውን እኩይ ስራዎች በገሀዲ ቁጥር ሶስት ዘርዝረው ያቀረቡ ሲሆን መጽሀፉ ህወሀትንና ህወሀትን ሲመሩ የነበሩ ሰዎችን ታሪክ የሚያቀርብ ፣ ይዘቱም በህወሀት ሰዎች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ መደናገጥ የፈጠረ ነው ተብሉአል።

የዜና ምንጮቻችን አክለውም የህወሀት ባለስልጣናት በቅርቡ "የ ገሀዲን ጎርፍን በምን እናግደው" በሚል አጀንዳ ተሰብስበው እንደነበርና አስገደን እንክሰሰው ወይንስ አንክሰሰው በሚል ጭቅጭቅ ላይ ሰንብተው እንደነበርና "ጸሀፊውን በህወሀት ደረጃ እንክሰስ፣ ህወሀት ክሱን ይመስርት" የሚል ሀሳብ የቀረበ ቢሆንም "እንደዚያ ማድረጉ ለመጽሀፉና ለጸሀፊው ትልቅ እውቅና የሚሰጥ ነው" በማለት የተቃወሙም እንደነበሩ ተመልክቱአል።

እንደዘገባ ምንጮቻችን ሪፖርት የትግራይ ፖሊስ አቶ አስገደን ለአንድ ቀን ይዞ ካሰረ በሁዋላ በሶስት ሺ ብር ዋስትና የለቀቃቸው የታወቀ ሲሆን፣ ከመቀሌ ከተማ እንዳይወጡ በማዘዝም የቁም እስረኛ አድርጓቸዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት አቶ አስገደን በስልክ በማነጋገር መጽሀፉ የህወሀት ሰዎችን በከፍተኛ ደረጃ ያስደነገጠና በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ አሁን በቁም እስር ላይ እንደሚገኙና መቼ ፍርድ ቤት እንደሚቀርቡ እንደማያውቁ መናገራቸውን ዘግቡአል።

የአረና ትግራይ ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ አስገደ በቅርቡ የኢፈርት ኩባንያዎች የጥቂት ግለሰቦች መበልጸጊያ እንጅ የትግራይ ህዝብ ንብረቶች አይደሉም በማለት መናገራቸው ይታወሳል።

## ከስራ የተባረሩ የቴሌኮሚዩኒኬሽን ሰራተኞች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ስጋት እንደነበረባቸው፣ ከገለጹ በኋላ፣ የኮሙዩኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ተብየው በተለያየ አጋጣሚና በተወካዮች ምክር ቤት «አንድም ሠራተኛ ሥራውን አያጣም፤» በሚል ተናግሮ እንደነበር እንደማይዘነጉት ገልጸዋል።

በትምህርትና በልምድ ያካበቱትን እውቀት በመጠቀም ለአገራቸው ዕድገት የበኩላቸውን ድርሻ እያበረከቱ እንደነበር የተናገሩት ወይዘሮ፣ ሚኒስትር ተብየው በተወካዮች ምክር ቤት አባላት ፊት የገባው ቃል ታጥፎና፣ የሥራ ዋስትና መብታቸውን በሚጥስና ፍፁም ሕገወጥ በሆነ መንገድ ከሥራ መባረራቸው ፣ ሐዘናቸውን እጥፍ ድርብ እንዳደረገባቸው ገልጸዋል።

በመጨረሻም ኢትዮ ቴሌኮም የወሰደው ዕርምጃ በመላው አገሪቱ የሚገኙትንና በሺዎች የሚቆጠሩ የድርጅቱን ሠራተኞች ከነቤተሰቦቻቸው ከፍተኛ የሚባል ችግር ውስጥ የጣለ መሆኑን የገለጹት ወይዘሮ፣ ከሥራ ገበታቸው ሊያፈናቅላቸው የቻለው ምክንያት ምን እንደሆነ ሳይነገራቸው በደፈናው «ተሰናብታችኋል» መባላቸው ዘረኛውና ግፈኛው የወያኔ አገዛዝ በዜጎች ላይ የሚያደርሰውን ገደብ ያጣ በደል ያመለክታል በማለት ተናግረዋል።

በተመሳሳይ መልኩ አንድ የአስተዳደር ክፍል ሰራተኛ ቴሌ የሚከስር መሥርያ ቤት ሳይሆን በየዓመቱ ትርፉ እየጨመረ የሚሄድ መስሪያ ቤት በመሆኑ ያለውን ሠራተኛ ማባረር ሳይሆን ተጨማሪ መቅጠር እንደሚችል በግልጽ እየታወቀ ሕገወጥ በሆነና የግል ፍላጐትና ጥቅም ላይ ተመስርቶና፣ አሠራሩም በጎሳ፣ በድርጅት አባልነት፣ በሙስና የተዘፈቀ በመሆኑ መፍትሄው ከዚህ የወያኔ ኢህአዴግ አገዛዝ ልንላቀቅ በምንችልበት መንገድ ላይ መሳተፍና የበኩላችንንም አስተዋጽኦ ማድረግ ብቻ ነው ማለታቸው ታውቋአል።

ቴሌ ውስጥ በነባርም ሆነ በአዲስ ተቀጣሪነት የተመደቡት ሠራተኞች ከተባረሩት ሠራተኞች በምን መመዘኛ ተሽሎ እንደተገኘ ግልጽ ካለመሆኑም በላይ፣ በትምህርት ዝግጁነት፣ በሥራ ልምድ፣ በሥነ ምግባርና በሥራ አፈጻጸም ብቃት ብልጫ ያላቸው ሠራተኞች ሳይመደቡ በሁሉም ነገር ዝቅተኛ ነጥብ ያላቸውና በዕድሜ የገፉ ሠራተኞች ሳይቀር መመደባቸው ታሪክ ወደፊት የሚያወጣው ነገር ይሆናል በማለት የአስተዳደር ክፍል ሰራተኛው ተናግረዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በቅርቡ ከወታደራዊ ሃይል አሰናበትኳቸው ያላቸውን ጀነራሎች ሳይቀር በኢትዮ ቴሌ ኮም መስሪያ ቤት ውስጥ ቁልፍ የስልጣን ቦታዎች መመደቡና እነኝህም ጀነራሎች የትግራይ ብሄር ተወላጆች እንደሆኑ ቀደም ብለን መዘገባችን ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz**
**<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz**
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz**
**እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። <u>ማሳሰብያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org